**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

የካቲት 27፣ 2004 ዓም

# በጋምቤላ ሜካናይዝድ ኃይል ተሰማራ

### ❖ ኃይለማርያም ደሳለኝና ኦሞት ኦባንግ ደቡብ ሱዳንን አስጠነቀቁ
### ❖ ሦስት የጥበቃ ኃይሎች ተገድለዋል፣ አንድ ቆስሏል

በጋምቤላ ክልል የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በርካታ ወታደሮችንና ብረት ለበስ የጦር መሳሪያ በማሰማራት አውጫጪኝ እያካሄደ እንደሆነ ተሰማ። የአገዛዙ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የክልሉ ፕሬዚዳንት ወደ ደቡብ ሱዳን አመሩ። ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች ጥቃት ሲፈጽሙ የኢታንግ ወረዳ መምህራን ስራ ማቆማቸው የክልሉን ውጥረት መባባስ እንደሚያሳይ ተዘገበ።

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የመረጃ ምንጮች ከስፍራው የላኩት መረጃ እንደሚያመለክተው በክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወታደሮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች እንዲሰማሩ የተደረገው በክልሉ ያለው ችግርና ውጥረት የህወሃት/ኢህአዴግን አገዛዝ በከፍተኛ ደረጃ ስላሳሰበው ነው። ከጋምቤላና ከደቡብ ሱዳን የመረጃ ምንጮቻችን የላኩትን ዘገባ በንዑስ ርዕሶች ከፋፍለን አቅርበነዋል።

## “ሽፍቶቹ ስድስት ወይም ሰባት ይሆናሉ”

እንደ መረጃ ምንጮቹ ገለፃ የህወሃት/ኢህአዴግ “ነፍጥ አንጋቾች” በብረት ለበስና በከፍተኛ መኮንን በመመራት በየወረዳውና በየቀበሌው ህዝቡን እየሰበሰቡ አውጫጭኝ ጀምረዋል። **“ሽፍቶቹ ስንት ናቸው? ስማቸውስ?”** በሚል ለቀረበላቸው **“ሽፍቶቹ ስድስት ወይም ሰባት ይሆናሉ”** በማለት አንድ አዛውንት መልስ ሰጥተዋል። ሌላ አዛውንት በበኩላቸው **“ሽፍታ የሚባል ነገር ሰምቼ አላውቅም፡፡ ለመሆኑ ሽፍታ ማለት ምን ማለት ነው?”** በማለት ጥያቄን በጥያቄ  መልሰዋል።

አስገራሚ መልስ የተባለውና “የነፍጠኞቹ” መሪ መኮንን ያናደደው ያንድ አዛውንት መልስ ነበር። በስፍራው የነበሩ የዓይን እማኞችን በመጥቀስ መረጃ ያቀበሉን እንዳብራሩት አዛውንቱ አማጺያኑን አስመልክቶ ለተጠየቁት ሲመልሱ **“አንድ ቀን ከጠዋት እስከማታ ተሰልፈው ሲሄዱ ዋሉ፡፡ በጣም ብዙ ናቸው፤ ውሃ ለመቅዳት ወንዝ የወረዱ ሴቶችም አይተዋቸዋል፡፡ የሚሄዱት ወደተለያየ አቅጣጫ ነበር፤ ታጥቀዋል፤ ሙሉ የወታደር ልብስም ለብሰዋል”** ነበር ያሉት። ሕዝቡ ከአማጺያኑ ጋር እንዳይተባበር በማስጠንቀቅ **“ለሽፍቶቹ ምንም ዓይነት መጠለያ እንዳታደርጉ፤ ሲመጡም ምግብ እንዳትሰጡ”** በማለት ነዋሪውን ያስጠነቀቁት የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ተወካዮች የተሰጣቸው መልስ **“ደኑ መጠለያቸው ነው፤ ጫካው ደግሞ ምግብ ሙሉ ነው”** የሚል እንደነበር ተዘግቧል፡፡

የአገዛዙ ከፍተኛ መኮንን በተሰጣቸው መልሶች በመናደድ **“እኔ ጊዜዬን ማጥፋት አልፈልግም”** በማለት ንዴታቸውን ሊቆጣጠሩ በማይችሉበት ሁኔታ መናገራቸውን ከዜናው ምንጮች ገለፃ ለመረዳት ተችሏል። ይኸው አውጫጭኝ ለወረዳ አስተዳደሮች ተመሳሳይ ጥያቄ በማቅረብ ተካሂዷል።

**“ሽፍቶቹ እነማን ናቸው? ስማቸው ማን ነው? ከየትኛው ቀበሌ ወይም ሰፈር ናቸው? አርሶ አደሮች ቀለብ እንዲከለክሉዋቸው ለምን አላደረጋችሁም? አርሶ አደሮች እነማን እንደሆኑ እንዲጠቁሙ ለምን አላደረጋችሁም?”** ወዘተ የሚሉት ጥያቄዎች ለወረዳ አስተዳደሮች ከቀረቡት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። የጋራ ንቅናቄያችን የመረጃ ምንጮች እንደሚሉት “ነፍጠኞቹ” መኮንኖች በተመሳሳይ “በቂ” መልስ ባለማግኘታቸው የወረዳ አስተዳደሮቹን ኮንነዋል፤ በድክመትም ፈርጀዋቸዋል። ፖለቲካዊ ውሳኔ

እንዲወሰንባቸው የሚያስገድድ መመሪያ አዘል ሃሳብ አቅርበዋል። በዚሁ መሰረት በክልሉ ካሉት ዘጠኝ ወረዳ አስተዳዳሪዎች መካከል አብዛኞቹ ከኃላፊነታቸው ተባርረዋል። በዚሁ ሳቢያ አለመተማመን ነግሷል። በፖለቲካው መስመር በተፈጠረው አለመተማመን የተነሳ የፋኚዶ አስተዳዳሪን እንዲተኩ የተመረጡት ሰው "ነግ በኔ" በማለት ሹመቱን እንዳልተቀበሉት ለመረዳት ተችሏል። ሹመቱን አልቀበልም ባሉት ላይ የተወሰነው ውሳኔ ባይገለፅም ውሳኔው በፖለቲካው መስመር ውስጥ የተፈጠረውን ክፍተት አመላካች እንደሆነ የመረጃው ምንጮች ጠቁመዋል።

## የኢንቨስተሮች ስጋትና ተጨማሪ ጥቃት

በተከታታይ በጋምቤላ በደረሰው ጥቃትና ጥቃቱን ተከትሎ የወታደራዊም ሆነ የክልሉ ልዩ ሃይል ፍንጭ ማግኘት አለመቻላቸው የፈጠረው ስጋት በተለይም ካሩቱሪንና ሳዑዲ ስታርን ክፉኛ አሳስቧል። **ባለሃብቶቹ ከፍተኛና አስተማማኝ የሚባል የፀጥታ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ የእርሻ ኢንቨስትመንት በተለየ መልኩ የአካባቢውን ህዝቦች ትብብርና ልዩ ድጋፍ ስለሚጠይቅ በክልሉ አስተማማኝ ሰላም ማስፈን ካልተቻለ ለቀው ሊሄዱ እንደሚችሉ ማስጠንቀቃቸው ለአገዛዙና ለክልሉ ባለስልጣናት ራስ ምታት እንደሆነባቸው ምንጮቻችን ውስጥ አዋቂዎችን ጠቅሰው አመልክተዋል፡፡**በተለይም በሳዑዲ ስታር ውስጥ የሚሰሩ የውጪ አገር ዜግነት ያላቸው ከፍተኛ የግብርና ባለሙያ ለደህንነታቸው በመስጋት ሳዑዲ ስታርን መልቀቃቸውንና ተጨማሪ የሥራ ባልደረቦቻቸውም በተመሳሳይ ከስጋት የተነሳ ለመልቀቅ በዝግጅት ላይ እንዳሉ በስፍራው የሚሰሩ ለኢኢ.ጋን የመረጃ ሰዎች አስታውቀዋል።

ተሽከርካሪዎችን በነፃነት ማንቀሳቀስ አለመቻሉ እያስጨነቀ ባለበት በአሁኑ ሰአት፣ እሁድ የካቲት 25 ቀን 2012 ዓም ከቀኑ ስምንት ሰዓት አካባቢ ማንነታቸው ያልታወቀ ታጣቂዎች ጉዳት ማድረሳቸው ታውቋል። ከስፍራው በደረሰን ዘገባ መሰረት ጥቃቱ የተፈፀመው ወደ ካሩቱሪ ሰፊ እርሻ በሚያስገባው መንገድ በጥበቃ ስራ በተሰማሩ ላይ ነው። በጥቃቱ ሶስት የጥበቃ ጓዶች ሲገደሉ፣ አንድ ቆስሏል። ጥቃት ፈፃሚዎቹም ማንነታቸው ሳይታወቅ ተሰውረዋል።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደተናገሩት ከጥቃቱ በኋላ የፖሊስና የልዩ ጥበቃ ኃይል በሥፍራ ተገኝተው ጥቃቱ በተፈፀመበት አካባቢ ቅርበት ያላቸውን ሰብስበው አስረዋል። የታሰሩትን ሰዎች ብዛት ያልገለፁት እኚሁ ክፍሎች ጥቃቱ ከተከናወነ በኋላ መተራመስና መደናገጥ መከሰቱን ተናግረዋል። ግድያው ከየትኛው ወገን ነው የሚለው ጥያቄ ማስነሳቱ ምንጮቻችን በመግለጽ ሲያብራሩም እንዲህ ዓይነቱ ግድያ መበራከት የክልሉን ሕዝብ ከፍተኛ ስጋት ላይ መጣሉን ጠቁመዋል፡፡

## ማስጠንቀቂያ ለደቡብ ሱዳን መንግስት

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝና የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ኦሞት ኦባንግ ከክልሉ ፀጥታ ጋር በተያያዘ ባለፈው ሳምንት ወደ ደቡብ ሱዳን አምርተዋል። በደቡብ ሱዳን የኢኢ.ጋን የመረጃ ሰዎች ከስፍራው እንደዘገቡት ሁለቱ ባለስልጣናት ጁባ ሲገቡ ከፍተኛ ጥበቃ ነበር።

ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት በጋምቤላ የኦኙዋክ ብሄር አባላት ላይ የተፈፀመውን ጭፍጨፋ በመሸሽ ወደ ደቡብ ሱዳን የገቡ ሰባት ሺህ የሚጠጉ የኦኙዋክ ስደተኞች ጁባ ስለሚኖሩ አደጋ ይፈጠራል የሚል ስጋት ነበር። ስደተኞቹን ፍርሃቻ በልዩ ጥበቃ ጁባ የገቡት የአቶ መለስ መልዕክተኞች፣ የደቡብ ሱዳንን ባለሥልጣናት እንዳስጠነቀቁዋቸው ታማኝ የመረጃ ምንጮቻችን ተናግረዋል።

**ከሁለት ወር በፊት የኑዌርና የሙርሲ ብሔር አባላት ተጋጭተው ከሁለት ሺህ የማያንሱ ሰዎች መሞታቸውን በማስታወስ ለደቡብ ሱዳን ባለስልጣኖች ማስጠንቀቂያ የሰጡት አቶ ኃይለማርያም፣በጋምቤላ እየተፈፀመ ያለውን ጥቃት በመደጋገፍ መቆጣጠር ካልተቻለ የደቡብ ሱዳን አኙዋክ አባላትን ምድር አልፎ ወደ ጅቡቲና ወደ ኬንያ የሚዘረጋውን የነዳጅ መስመር ግንባታ ሊያስተጓጉለው እንደሚችል በመጠቆም አስጠንቅቀዋል፡፡**

በደቡብ ሱዳንና በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ መካከል በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በወታደራዊ መስኩ ያለው ግንኙነት አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል በሚያስጠነቅቅ መልኩ ማሳሰቢያውን የሰጡት አቶ ኃይለማርያም፣ **በደቡብ ሱዳን መሳሪያ የታጠቁ ነዋሪዎች በሙሉ ትጥቅ እንዲፈቱ እንዲደረግ በአጽንዖት ተናግረዋል፡፡ በደቡብ ሱዳን የጋራ ንቅናቄያችን የመረጃ ምንጮች እንደዘገቡት፣ የደቡብ ሱዳን መንግሥት**

**ቁጥጥሩን እንዲያጠብቅ፣ በድንበር አካባቢ ክትትል እንዲያደርግ፣ ከደቡብ ሱዳን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅም አንፃር ትብብሩን እንዲያሳይ አቶ ኃይለማሪያም ተማፅነዋል፡፡**

## "እባካችሁ ወገኖቼ እርዱኝ"

የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦሞት በስደት ጁባ ከሚኖሩት የአኙዋክ ብሄር አባላት መካከል ከእርሳቸው ጋር አንድ መንደር ያደጉ ጓደኞቻቸውን (የመንደራቸውን ሰዎች) አስጠርተው ከአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር በመሆን አነጋግረዋል። ከጁባ በቀጥታ ያነጋገርናቸው ክፍሎች እንዳስታወቁት፣ አራት የሚሆኑ የአቶ ኦሞት መንደር አብሮ አደጎች አቶ ኦሞትን ለማነጋገር በሄዱበት ወቅት ከፍተኛ ፍተሻ ተካሄዶባቸዋል፡፡ ከፍተሻውም በኋላ በጋምቤላ ጥቃት እየፈፀሙ ናቸው ስለሚባሉት የአኙዋክ ብሄር አባላት ማንነት እንዲናገሩ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል።

**"ከአሜሪካ በመምጣት ድጋፍ የሚሰጧቸው እነማን ናቸው? ክልላችንን ሊያተራምሱ የተነሱትን ንገሩን፣ችግሩ ከቁጥጥር ውጪ ከሆነ በክልሉ የተጀመረው የባለሃብቶች እንቅስቃሴ አደጋ ላይ ይወድቃል"** በማለት አብሮ አደጎቻቸውን ቢማፀኑም **"አውቃለሁ" በሚል የሚመልስ አልተገኘም፡፡** ያነጋገርናቸው ውስጥ አዋቂዎች እንዳሉት የጠበቁትን ምላሽ ያላገኙት **አቶ ኦሞት "ከዛሬ ጀምሮ እርዱን" በማለት የመንደራቸውን ሰዎች ለምነዋል፡፡**

**የአኢጋን የመረጃ ክፍሎች የላኩት ሰፊ መረጃ እንዳመለከተው አቶ ኦሞት ላነጋገሩዋቸው የመንደራቸው ልጆች በወር እስከ 1000 ዶላር ደሞዝ እንደሚከፈላቸው ቃል በመግባት የየእለቱን የአኙዋክ ወንድሞቻቸውን እንቅስቃሴ በመከታተል ጁባ ላሉ የመረጃ ሰዎች ሪፖርት እንዲያቀብሉ ጠይቀዋል። በጁባ ካሉት የደህንነት ሰዎች መካከል አራቱን እንዲተዋወቁ መደረጉን የጠቆሙት መረጃዎቻችን፣አራቱም የትግራይ ተወላጅና በጁባ በኮንስትራክሽንና በታላላቅ ንግድ የተሰማሩ በባለሃብትነት የሚታወቁ መሆናቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡** ከትውውቁ በኋላ አቶ ኦሞት **"የእኛ ስኬት እናንተ ናችሁ፤ወገኖቼ እርዱኝ"** በማለት ተማፅነዋል።

አቶ ኦሞት ከሁለት ወር በፊት ከተካሄደባቸው ግምገማ በኋላ በደቡብ ሱዳን የኢትዮጵያ አምባሳደር እንዲሆኑ ሲነገራቸው ጭፍጨፋውን በመሸሽ ወደ ደቡብ ሱዳን የገቡትንና የደቡብ ሱዳን የአኝዋክ ጎሳዎችን በመፍራታቸው ሹመቱ በስምምነት ሳይፀድቅ እንደቀረ ምንጮቻችን አስታውሰዋል።

## ገንዘብ የለም፣ የኢታንግ መምህራኖች ሥራ አቆሙ፤

በሌላ ዜና የኢታንግ ወረዳ መምህራኖች ከአራት ወራት በላይ ደሞዝ ባለማግኘታቸው ስራ አቁመዋል።መምህራኑን ዋቢ ያደረጉት ምንጮች መምህራኑ ስራ ከማቆማቸው በፊት ባለፈው ዓርብ **የካቲት 23 ቀን 2012 ዓም ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር "ያለ ደመወዝ መስራት አንችልም"** የሚል ደብዳቤ ለመጨረሻ ጊዜ አስገብተዋል።

በተለያዩ ጊዚያት "ያለ ደመወዝ መስራት አንችልም" በማለት ጥያቄ ሲያቀርቡ "የአገሪቱ ችግር ነው፤የተለያዩ ችግሮች አሉብን" የሚል መልስ ይሰጣቸው እንደነበር ያስታወሱት መምህራኑ፣ አማራጭ በማጣት ስራቸውን በማቆም ወደ መጡበት ተመልሰዋል። የማስተማርና የመማር ሂደቱም መቋረጡን የአካባቢው ምንጮች አስረድተዋል። ይህ ጽሁፍ እስከወጣበት ዕለት ድረስ የተለወጠ ነገር የሌለ ሲሆን ከዚህ ሳምንት መጀመሪያ ጀምሮ ተማሪዎች ቤታቸው ውለዋል፡፡ መምህራኑ በሌሎች ክልልና ከተሞች ለመምህራንና ለሌሎች ሰራተኞች ደሞዝ ሳይቆም በጋምቤላ መምህራንና አንዳንድ ሰራተኞች ላይ የተፈፀመው ተግባር አግባብነት እንደሌለው በመጥቀስ አሁን ባለው ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ያለደመወዝ ይህንን ያህል ወራት ቢያሳልፉም በዚህ ሁኔታ መቀጠል የማይችሉበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ሥራቸውን አቁመው ወደመጡበት ለመሄድ መገደዳቸውን አስታውቀዋል፡፡

## ብረት ለበሱ ኃይል፤

በጋምቤላ የኢኮኖሚ ችግር፣ ውጥረት፣ የሙስና አደጋ፣ የመሬት ነጠቃና አስገድዶ ከቀዬ ማፈናቀል ተዳምሮ የፈጠረው ስሜት ቀደም ሲል በግፍ ከተፈፀመው ጭፍጨፋ ጋር ተዳምሮ ውጥረቱን እንዳባባሰው የሚስማሙ አስተያየት ሰጪዎች **"የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ እስካሁን ለተፈጸሙት ጥቃቶች አንዳችም ማስተባበያ በግልጽ ሳይሰጥ ልውካን ወደ ደቡብ ሱዳን መላኩ የጭንቀቱን መጠን የሚያሳይ ነው"**

ብለዋል። በሌላም በኩል ህዝብ ሰብስቦ የሚሰጠው መልስ ስርዓቱ ከህዝብ መለየቱን የሚያመላክት እንደሆነ ጠቁመዋል።

የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ወታደራዊ ኃይሉን በማጠናከር የጋምቤላ መኩድ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በታንክና በብረት ለበስ መሳሪያ እንዲጠበቅ መደረጉን ያመለከቱት የመረጃ ምንጮቻችን አቶ ኦሞት **"እኔ ከታሰርኩ መሳሪያና ወታደር የሰጡኝ አቶ መለስም መታሰር አለባቸው" ማለታቸው ከተሰማ በኋላ በተከታታይ የተፈፀሙትን ጥቃቶች አስመልክቶ ሃላፊነት የወሰደ አካል የለም። አገዛዙም ሆነ ክልሉ በይፋ ሲያስተባብል አልተሰማም።**

**ብረት ለበስ ኃይል በማሰለፍና ህዝብ በመሰብሰብ አውጫጭኝ እያካሄደ ያለው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ወደ ስልጣን በመጣበት መንገድ ፈተና ስለገጠመውና ርምጃው ወደ ሌሎች ክልሎች እንዳይስፋፋ በዲፕሎማሲና በማባበል እንቅስቃሴውን ለመግታት ሌት ተቀን እየሰራ መሆኑን ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸው ለአኢጋን ተናግረዋል። ብረት ለበስ መሳሪያና ሰፊ ቁጥር ያለው ወታደር ማሰማራቱ የዚሁ የጭንቀቱ ማሳያ እንደሆነም ጠቁመዋል።**

## የፖለቲካው መስመር የገጠመው አለመተማመን፤

በጋምቤላ የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ በሚል የፖለቲካውን አመራሮች በመገምገም በየጊዜው የሚከናወነው የሹም ሽር የፈጠረው አለመተማመን ሌላውና ዋና ሊባል የሚችል ቀውስ **ሆኗል። ተጠርጥረው ከኃላፊነት በሚነሱና አዲስ ሹመት በሚሰጣቸው ተተኪ ባለስልጣኖች መካከል የፓርቲ ስራ ለመስራት የማያስችል ልዩነት መስተዋሉን የአኢጋን የሚዲያና ህዘብ ግንኙነት ግብረኃይል ያሰባሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ።** ከላይዋ ሰላም የምትመስለው ጋምቤላ ውስጧ ግን በውጥረትና በፖለቲካ ችግር የተቀፈደደች መሆኑን ታውቋል።

**በተመሳሳይ የደቡብ ሱዳን የአኙዋክ ጎሳ አባላት ከከፍተኛ የፖለቲካና የመከላከያ ስልጣን ጀምሮ በክልሉ በስፋት ስለሚንቀሳቀሱ የደቡብ ሱዳንን አቋም የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በጥርጣሬ መመልከቱ ሌላው የፖለቲካ ክፍተት መሆኑን፣ የደቡብ ሱዳን መንግስትም የህወሃት/ኢህአዴግን አገዛዝ ለማስደሰት በሚል በራሱ ጎሳዎች ላይ ሊወስደው የሚችለው ርምጃ ስለመኖሩ የተሰማ ፍንጭ አለመኖሩ ሌላ የፖለቲካ ክፍተት እንዳይፈጠር ተሰግቷል።**

አቶ ኦሞት "እኔ ከታሰርኩ..." ካሉ በኋላ የግምገማው ውጤት ተገልባጦ በሃላፊነታቸው ለስድስት ወር እንዲቆዩ መደረጉ የፈጠረውን ጥርጣሬ ዓይነት በደቡብ ክልልም ተከስቷል። በክልሉ የፓርቲ ግምገማ ርዕሰ መስተዳድሩ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ **"እኔ ከተከሰስኩ ወይዘሮ አዜብ መስፍንም መከሰስ አለባቸው"** በማለት በኪራይ ሰብሳቢነትና በሙስና የገመገማቸውን ጉባኤ ረግጠው መውጣታቸው ይታወሳል።በግምገማው መጨረሻ አቶ ሽፈራው ከሃላፊነታቸው ወርደው በወንጀል እንዲጠየቁ የተወሰነውን ውሳኔ አቶ መለስ ሽረውታል። በዚህም ሳቢያ በደቡብ ክልል የፖለቲካ ውሳኔ ሰጪ አካላት መካከል አለመተማመን እንዲነግስ ማድረጉን የክልሉን ምንጮች ጠቅሰን መዘገባችን አይዘነጋም።

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

---

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነትን (media@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

